# ተው ሆዴ!

እንደ ሓምሌ ዳመና ዝናም ያረገዘ
ነገር ኣልተው ኣለኝ እየገዘገዘ...
ተው ኣታንጐራጉር፣ ተው ሆዴ፣ ተው ሆዴ
ነገር ማብጠልጠሉ ወይ ጉዴ! ወይ ጉዴ!



ነገር ማንጐራጐር ከቶ ጥቅም የለው
መልካምና ደጉን ኣብረን ልንችለው፣
ተው ተመከር ሆዴ፣ ኣትበል ‘መረረኝ!’
ቢከፋ፣ ቢደላ፣ ካላንተ ማን ኣለኝ?



እንደ ሓምሌ ዳመና ጠቁሮ እንደ ጨለመ
ኣስቸገረኝ ሆዴ ነገር እያለመ...
ቆሎ፣ ጥሬ ቀምሰህ ኣታርፍም ወይ ከቶ?
ተው ዓርፈህ ተቀመጥ ታስረህ በቀበቶ!

ገ/ኢ. ጐርፉ።